# አንድነት

መተሳሰብ መረዳዳት
ሁልጊዜ ተግቶ
ያለመሰልቸት መሥራት፣
መዋደድ መፈቃቀር
ለወገን ለዘመድ አዝማድ መቆርቆር
ዘወትር አንድነትን ማጠናከር።

የአገር ልጆች ተባብለን
በአንድ ዓላማ ተሣሥረን
ሁላችንም በአንድነት
መተባበርን ፈጥረን፣
ምናለ ባንድነት ሆነን ብንሠራ
ቁምነገር ፍሬ ብናፈራ
በወገናችን ሕይወት ብንዘራ፣
ጊዜ መሄዱ ላልቀረ
ብቻ ማሳው ላይታረስ ጦም አደረ።

ክፋት ምቀኝነትን ወዲያ ትተን
እርስ በርሳችን ተስማምተን፣
ሳናሰልስ ብናስብ
ምናለ ጥሩ ጥሩ ምርትን ብንሰበስብ፣
ምናለ የቂም በቀል
መድረኮችን ባናሰፋ
እርስ በርሳችን ባንጋፋ፣
የአገሬ ሰው ሞኝ ሆነ
በአልባሌ ድካም ባከነ
አንድነትን ለመፍጠር ቦዘነ፣
መተባበሩ እንደሚጠቅመው ሳይረዳ
በመበታተኑ ተጎዳ።

ምናለ በስምምነት
አንድነትን ብንመሠርት
የዕውቀት አድማሳችን ቢጎለብት፣
ወደኋላ መለስ ብለን
ታሪክ የሚነግረንን ተገንዝበን
ጥሩ ባሕላችንን እያስታወስን
መልካም መልካሙን እየመረጥን፣
ወገን ከወገኑ ቢረዳዳ
አንዱ ሌላውን ባይጎዳ፣
መከባበር መቀራረብ ቢኖርበት
ማሕበራዊ ኑሮአችን ቢጎለብት፣

ልማት ዕድገቱ ቢፋጠን
አዳዲስ ትልም ቢወጠን፣
ችግሩ ሁሉ ቢወገድ
በዕድገት ጎዳና ብንራመድ፣
ወገን ሁሉ ቢሻሻል
እንዴት ማየቱ ደስ ይላል።

በል ወገኔ ልምከርህ
ከንቱ እንዳይቀር ድካምህ፣
የብቸኝነትን ኑሮ ተውና
በግል ጥቅም ሳትማረክ
ለአንድነትህ ትኩረት ስጥና፣
ሥራህን በዕውነት ብትሠራ
ፍላጎት ምኞትህ ሲጎበራ፣
ያኔ እድገትህ ሁሉ በጣም ያምራል
ችግርህ ሁሉ ከናካቴው ይወገዳል፣
በዘላቂ አለኝታህ ስትመካ
ለዘለዓለም ኑሮህ ሲሳካ፣
የመተባበርህ ዕውነተኛ ምሥጢሯ
መከባበር መተሣሠር መፈቃቀድ
አንድነት ነው ተግባሯ።

ዓለማየሁ አስፋው/ ቶሮንቶ